# ተመስጦ

ተመስጦ ምን ማለት ነው?

አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ተመስጦ ሲባል፦ ይህ ሰው ነገሩን በቅርበት እየመረመረ፣ እያጠናው፣ እየፈተሸው፣ ጥልቀቱን ለማየት እየተንተነው ነው ማለት ነው።

ተመስጦ ማለት በሀሳብ ወይንም በመንፈስ ወደ ጥልቁ ምሥጢር መንጠቅ ማለት ነው። ይህም ከተለመደው የዕውቀት ዓይነት ወደከፍተኛው ደረጃ መድረስ ነው። ዕውቀቱም ከስሜት በላይ የሆነና ሁሌ አዲስ የሚሆን የመንፈስ ተድላና ደስታ ነው። በዚህ ዕውቀት ውስጥ መንፈሳዊ ምግብና ደስታ አለ።

ተመስጦ፣ አእምሮን፣ ልብና መንፈስን ከላይ ብቻ የሚገኘውን አምላካዊ ዕውቀት ለመቀበል ማዘጋጀት ማለት ነው። ወይንም በውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለማነሳሳት መፍቀድ ማለት ነው።

ለተመስጦ ፀጥታ፣ እርጋታ፣ ስሜትን መግዛትና መንፈስን ከሚያውኩ ማናቸውም ነገሮች መታቀብ አስፈላጊዎች ናቸው።

የሰው ስሜት ከውጪያዊ ሁከቶች ነፃ ሲሆን፣ ከሥጋዊ ሀሳብ ሲላቀቅና፣ ለመንፈሳዊ ስጦታዎች ራሱን ሲያዘጋጅ ተመስጦው ጥልቅና ስኬታማ ይሆናል።

ለተመስጦ ስኬት የሚረዳው አንድን ነገር ለማወቅ ያለህ ፍላጎትና አምላካዊ ነገር ላይ ማተኮር ነው።

በመቀጠል በዝርዝር ልናያቸው የሚያስፈልጉ ብዙ የተመስጦ ክፍሎች አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በመዝሙር፣ በዜማ ተመስጦ ሊመጣ ይችላል። ወይም በሥነ ፍጥረት ውበትና ጥበብ፣ በሰማያትና በመላእክት፣ በሞት፣ በፍርድና ከዚያ በኋላ ባሉ ሁኔታዎች መነሻነት ሊጀምር ይችላል። በድርጊቶች፣ በቅዱሳን ሕይወት፣ በውሱን ወይም በአጠቃላይ ሥነምግባሮች፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት የሚመጣም ሊሆን ይችላል። ሌላ ታላቅ የሆነና በእግዚአብሔር ድንቅ ባህርያት ለምሳሌ ወሰንየለሽነቱን፣ እውነተኛነቱን፣ ጸጋውን በማሰብ መመሰጥም አለ። በአጠቃላይ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። የሚጠቅሙትን መንፈሳዊ ነገሮች ለመምረጥ በቁሳዊ ነገሮች ላይ እንኳን ሰው ሊመሠጥ ይችላል።

## የተመስጦ ዓለሞች

### መጽሐፍ ቅዱስ

በእግዚአብሔር አነሳሽነት የተነገሩና የተጻፉት ቃላት መንፈስ የሆኑና በትምህርት በአካል ግዝፈው የሚታዩ ናቸው። ፊደሎቹ ሳይሆኑ በውስጣቸው ያለው መንፈስ ደግሞ ሕይወት የሚሰጥ ነው። (2 ቆሮ 3:6)። ለዚህ ነው ጌታችንም «ሕይወትን የሚሠጥ መንፈስ ነው» ሲል የተናገረው። (ዮሐ 6:63)።

በውስጡ ሉል /የባህር ዕንቁ/ እንዳለው ቅርፊት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትም ጥልቅ የሆነ ምሥጢርን በውስጣቸው ያመቁ ናቸው። ዕንቁው የቃላቱ መንፈስ ነው። ስለዚህ በቃላቱ ወይም በቅርፊቱ ብቻ አትርካ። ሽፋኑን ገላልጠህ ውስጣዊውን ሉል ውሰድ። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነትና እንደ ቅዱስ ዳዊት «ዓይኖቼን ክፈት፣ ከሕግህም ተዓምራትን አያለሁ» እያልክ በምትጸልየው ጸሎት ነው። (መዝ 118:18) ወይም «አቤቱ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን አባክህ ግለፅ» ብሎ ስለ ደቀመዝሙሩ ግያዝ እንደጸለየው ዐይኖቹን እንዲገለጠለት ኤልሳዕ በቅዱሳን የምልጃ ጸሎት የሚገኝ ነው። (2 ነገ 6:17)።

ተመስጦ በመንፈስ ቅዱስ ግብር የሚመጣ የአእምሮ ብሩህነት ነው። በዚህ ብርሃን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት ሽፋናቸውን ገልጦ ምሥጢሩን መፈለግና በጥልቀት



www.ethiopianorthodox.org

መረዳት ይቻላል:: ይህም ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመመሰጥ በእግዚአብሔር ገላጭነት የተቀመጠውን አምላካዊ እውነት ለማግኘት መጣር ነው:: «በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው::» (ሉቃ 24:45)::

በእውነት አምላክ ሆይ በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን:: አእምሮአችንን፣ ልባችንንና ሀሳባችንን እንዲያበራልን ከዚያም ተነስተን «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን ማስተዋል እንድንችል እንፈልጋለን:: (ራዕ 2)

እንደዚሁ አንተም በሀሳብህ፣ በልብህ፣ በመንፈስ የምታደርገውን ጥረት ሁሉ አእምሮህ ብሩህ ሆኖ አባቶችህ የተቀበሉትን ለመቀበል የበቃህ ያደርግህ ዘንድ እንደምታቀርበው ጸሎት የሚቆጠር ነው:: የአንተ ሥራ አእምሮህን ዝግጁ አድርገህ እግዚአብሔር ከጥልቁ ዕውቀትና ከማስተዋሉ እንዲሞላበት ማቅረብ ነው:: ማድረግም ያለብህ ልብህን መክፈትና ጌታ ገብቶ ከአንተ ጋር እራት እንዲበላ መፍቀድ ነው:: (ራዕ 3:20):: አዎን አንተ እና እኔ ከሰማይ ከወረደው ሕብስት ጋር እንበላለን:: (ዮሐ 6:33):: በዚህ የሕይወት ሕብስትና ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል መኖር እንችላለን:: (ማቴ 4:4)

በተመስጦ ውስጥ ሕሊናህ የተጓዘው የመጀመሪያው እርምጃ ለመንፈስ ቅዱስ በር የመክፈት ያህል የሚቆጠር እርምጃ ነው::

ለዚህ ነው አባቶች ተመስጦን በጥልቀት እየተመለከቱ:- «ከሰዎች ጥረት በላይ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ» የሚሉት:: ቅዱስ ዳዊትም የሚለው ይህንኑ ነው:: «አፌን ከፈትሁ፣ አለከለከሁም:: ወደትእዛዝህ ናፍቄአለሁና» (መዝ 118:131)::

ተመስጦ በመንፈስ ቅዱስ የሚሠጥ የጥናት ክፍለ ጊዜ ነው:: በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ ሊሰጥህ የወደደውን እንዴት መቀበል እንደምትችል የምትለማመድበት መንገድ ነው::



ተመስጦ አእምሮ አንድን ነገር ለመረዳት /ለማወቅ/ ከሚያደርገው ጥረት በላይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚናገረው በዕውቀትና በችሎታ መደገፍም አይደለም:: «በራስህ ማስተዋል አትደገፍ» (ምሳ 3:5)

ዕውቀትንና ፍልስፍናን ሊያመጣ የሚችለው ምሁራዊ አስተሳሰብ እንኳን ቢሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሌለበት ተመስጦን ሊያመጣ አይችልም:: በምሁርና በአምላኮ ውስጥ ባለ ሰው መካከል ሠፊ ልዩነት አለ:: በሚያጠናና በሚመሠጥ፣ መጻሕፍትን በሚመረምርና ከመንፈስ ቅዱስ በሚቀበል ሰው መካከልም እንደዚሁ ልዩነት አለ:: ተመስጦ ሀሳብ ብቻ አይደለም:: ሀሳብን ከልብ ጋር አዋህዶ ልብን እንደመሳሪያ በመንፈስ እጅ መተውና ከእግዚአብሔር መንፈስ ለመቀበል መቃተት ነው:: በዚያን ጊዜ በመንፈስ ጥንካሬን ያገኘውን የቃሉን ጠንካራነት እንገነዘባለን:: ከዚህ በኋላ ወንድሜ ሆይ ትክክለኛው የአእምሮ ደረጃ ላይ ደረስኩ ብለህ እንዳትቆም:: ነገር ግን ሕሊናህን መንፈስ ጋር የመድረሻ መንገድ አድርገው:: መንፈስም የዕውቀት ሀብቶች ሁሉ ወዳለው ወደእግዚአብሔር ስለሚመራህ እርሱ ሁሉን ይሰጥሃል::

ንባቡ ውጪያዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ሰው ያለተመስጦ ብዙ ሊያነብ ይችላል:: መንፈሳዊው አንባቢ ግን ባነበባት ትንሽ ነገር የማይነጥፍ የተመስጦ ምንጭ ሊኖረው ይችላል:: ባነበበው ላይ ይመሰጣል እንጂ ብዙ ስለማንበብ አይጨነቅም::

ቃልም ሆነ አገላለጽ በእጅጉ ስለሚስቡት በዚያው ወደጥልቁ ገብቶ ሲመረምር ይቆያል:: «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ ትእዛዝህ ግን እጅግ ሠፊ ነው::» እያለ ከዳዊት ጋር ያመሠግናል:: (መዝ 118:96):: እግዚአብሔርም ልቡን ይከፍትለትና በአንዲት ቃል ምንም ያህል ቢወስድለት የማያልቅ ትልቅ ሀብትን ያያል:: አሁንም በዚህ ከነቢዩ ጋር ደስ ይለዋል (ሐሴትን ያደርጋል::) «ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ» (መዝ 118:162)::

እንደመንፈሳዊው ልምምድ በቀን ቢያንስ አንድ ጥቅስ ለተመስጦ እንዲሆንህ ውሰድ:: ስታነበው ከዚህ በፊት ምንም



www.ethiopianorthodox.org

የልነካህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አገናዝብ:: በዚህ ሳትገደብ በዝግታ እያጠናኸው እንደዓለመ ተመስጦ ውሰደው:: በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ለሚሰጥህ ነገር እድል ስጥ:: ወይንም አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ታሪክ ውሰድና እንደዓለመ ተመስጦ ተጠቀምበት::

እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያደርገው ልዩ እንክብካቤም ሠፊ የተመስጦ ዓለም ነው::

እግዚአብሔር የሚወዳቸውን እነርሱም በፍጹም ወዳጅነት የሚያፈቅሩትን ከእርሱ ጋር የጠለቀ ሕብረት የነበራቸውን ቅዱሳኑን አስብ:: ወይም በቸርነቱ በትዕግስቱ መጠን የተንከባከባቸውን በዚህ ተጠቅመው ንስሐ የገቡ ኃጥአንን አስብ:: ሌሎች ልባቸው የደነደነ በቅንነቱ ያልተጠቀሙትንም እንዴት ይጠብቃቸው እንደነበረ አስታውስ::

የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችም ሊመስጡህ የሚችሉ ናቸው:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጥቅሶችን ማስታወስ መቻልም ሌላው ለተመስጦ የሚያነሳሳህ ነገር ነው:: እርስ በእርሳቸው እየተፈጸሙና እየተሟሉ ተመስጦ በጀመርክበት ጊዜ ሁሉ ጥቅሶችን ታገኛቸዋለህ:: እያንዳንዱ ቃል ልዩ ትርጉም ይሰጥሃል:: ሁሉም የተመስጦን አቅፍ አበባ ያበረክቱልሃል:: ከዚህ ጋር አያይዘህ «መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል አስታውስ (1ቆሮ 2:13)::

ይህን ብታደርግ ሙሉውን ቀን በመንፈሳዊ ሀሳብ ብቻ ትይዘዋለህ:: እነዚህ መንፈሳዊ ሀሳቦች ውስጥህን ሰርስረው ይገቡና ንጹሕ ሀሳብህ ንጽሕናን ይወልዳል:: ልብህ በተመስጦ የተሞላ እና ንጹሕ የእግዚአብሔር ቃል የሚሠራበት ይሆናል:: ተመስጦህ በራሱ በጸሎትህ ሰዓት እያጀበህ ከሰዎች ጋር እንኳን እያወራህ ባለህበት ሰዓት ወደቀናው ሊመራህ ኃይል ያገኛል:: አድማጮችህም ግብዝነት የሌለው ጥልቅ የሆነ ነገርህን ሁሉ ይረዱልሃል::



ተመስጦ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬም ይጠቅማል:: ተመስጦ ፡ በሀሳብ፣ በመንፈሳዊ ስሜት፣ በውስጣዊ እርካታ፣ በዕውቀት፣ በደስታ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ወደሕይወትህ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችም የማደግ ባህርይ አለው:: ስለዚህ የምታነበው መጽሐፍ ቅዱስም ይሁን የቤተክርስቲያን አባቶች ታሪክ /ገድል/፣ ራስህን በማንበብና በመመሠጥ ላይ ብቻ አትወስን:: ያነበብከውን ሁሉ ከሀሳብህ፣ ከልብህ ጋር አዋህደህ በተግባር አውለው::

ተመስጦን ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ሕብረትና ከሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት የምታሻሽልበት ማንገድ አድርገህ አስበውና በመንገዱ ለመጓዝ ራስህን አመቻች:: የምታነበው ሁሉ በጸሎት የተደገፈ ይሁን:: «ዐይኖቼን ክፈት ከሕግህም ተዓምራትን አያለሁ::» (መዝ 118:18) እንዳለ ዳዊት ተመስጦ አምላካዊ ገላጭነትን ይፈልጋል:: አንዳንዴ ሰው እግዚአብሔር በገለጸለት ምሥጢር ተገርሞ ሲያነበው ከዚህ በፊት ያላገኛቸው አዳዲስ ትምህርቶችንና ቀድሞ ሕሊናውን ያልሰቀሉትን ልዩ ምስጢራት ያገኛል::

መዝሙረ ዳዊትን ስታነብ ወይም ስትጸልይ ይህን የመሠለ ነገር ያጋጥምሀል:: ዘወትር በምትጸልየው ጸሎት ውስጥ በየዕለቱ አዲስ የሆነና ከዚያ በፊት ያላገኘኸው አምላካዊ ምሥጢር ሊገለጽልህ ይችላል:: እግዚአብሔር በሕሊናህ ውስጥ የሚበራ የብርሃን መስኮት ለአንተ ይከፍትልሃል:: ይህ ብርሃን በአንተ ዕውቀትና የአእምሮ ብቃት የመጣ እንዳይመስልህ:: ተመስጦህ ስታነብና ስትጸልይ እግዚአብሔር በአንተ ላይ ያዘነበው የማያልቀው ስጦታው ክፍል እንደሆነ እወቅ:: ጸሎት የተመስጦ ምንጭ ይሆንህና እራሱ በተመስጦ ይታጀባል:: በዚህ ዓይነት ጸሎት ውስጥ ቃላት ሁሉ ሠፊና ወሠን የለሽ ጥልቅ ምሥጢርን የያዙ መሆናቸው በየዕለቱ ይታያል::

የተመስጦ ልምድ ወይም ጸጋ ከሌለህ የቅዱሳን አባቶችን የተመስጦ ሕይወት የሚናገሩ መጻሕፍትን አንብብ:: ታላቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በማቴዎስ ወንጌል፣ በዮሐንስ ወንጌል፣ በሐዋርያት



www.ethiopianorthodox.org

ሥራና በአሥራ አራቱ የጳውሎስ መልእክታት ላይ እጅግ ብዙ የአንድምታ መጻህፍትን ጽፏል:: እነዚህ ሁሉ ተመስጦና ማብራሪያን የተሞሉ ናቸው:: ቅዱስ ዮሐንስ መጻሕፍቱን በተመስጦ ያብራራበትን ያስተማረበትን ብሎም የተማረበትን መንገድ መርምርና ተከተለው::

እንደዚሁ ከሌሎችም ቅዱሳንና ከሥራዎቻቸው ጋር ቆይታ አድርግ:: በተለይም በዚህ በትምህርታቸው ጥልቀት ብቻ ሳይሆን በተመስጦ እውቅና ካላቸው እንደማር ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ከመሳሰሉት አባቶች ብዙ ተማር:: ሥራዎቻቸውን እያነበብክ እንደተመሥጦ ትምህርት ቤት ተጠቀምበት::

በመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌያዊ ጽሑፎች ላይ ልዩ ተመስጦ የነበራቸውን አባቶች ሕይወት ለማንበብ ራስህን አለማምድ:: ምሳሌያትን ማንበብ፣ የነቢያትን መጽሐፍ፣ የሰሎሞንን መኃልያት ለመረዳት በጣም ጠቃሚ ነው:: የመሥዋዕቱን የስእለቱን፣ የበዓላቱን፣ በርኩሰትና በመንጻት መካከል ያሉትን ሕግጋት ሁሉ ሊመጣው ያለው ነገር ጥላ መሆን ለመረዳት ያስችልሀል (ቆላስ 2:17)

ምንም ጥቅም በሌላቸው ሁከትና ጭንቀት በበዛባቸው ተራ ነገሮች እንዳትጠመድና በመልካምና ጠቃሚ በሆኑ ነገሮች የተከበብክ እንድትሆን ተመስጦን በተግባር ልመደው:: ጥሩም ይሁን መጥፎ ባቀረብክለት ነገር ይወሰን እንጂ፤ አእምሮህ ለተመስጦ ፈጣን መሆኑን እርግጠኛ ሁን:: ከዓለማዊ ነገር፣ ወይም ከውስጥህ የቀረቡ የተለያዩ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ነገር ግን መምረጥ ያለብህ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ የሚጠቅመውን ብቻ ይሁን::

ይህ ጸጋ ለቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ለአንተም ለሁላችንም እንዲያውም ለኃጥአንም ጭምር የተሠጠ መሆኑን በውቀህ ልትጠቀምበት ያስፈልጋል:: የሚያስገርም የተመስጦ ችሎታ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: የሚያሳዝነው ግን በኃጢአት መሆኑ ነው:: ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች በአንድ የተለየ የኃጢአት ዓይነት ላይ መመሠጥና



አድናቆት ውስጥ መግባት ቀላል ነው:: ያ የሚያሰላስለውና የሚያስበው ኃጢአት ደግሞ ሀሳቡን፣ ስሜቱን ስለሚገዛው፣ በሕሊናው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል:: ይህ ብዙ ጸሐፊያን፣ ገጣሚያን እና የልብ ወለድ ደራሲያን የሚጠቀሙበት ዘዴ ማለት ነው::

የቅዱሳን የሆነው ግን በመንፈሳዊ ነገር ላይ ብቻ ያተኮረ ነው:: ስለዚህ በኃጢአት ውስጥ ሆነው በክፉ ሀሳብ የሚመሠጡት ሰዎች በንስሐ ቢመለሱና ይህን ጸጋቸውን ወደመንፈሳዊ መንገድ ቢቀይሩት አስገራሚ ውጤትይገኝበታል::

ከኃጢአተኝነት ወደንስሓና መንፈሳዊ እድገት የተመለሰውን ከዚያ በኋላ ኃጢአቱን ሁሉ ዘርዝሮ "The confessions" በሚለው መፅሐፉ ላይ የጻፈውን ቅዱስ አውግስጢኖስን እንደምሳሌ ማየት ይቻላል::

ማንበብ ተመስጦን ከሚያመርቱ መሳሪያዎች አንዱ ነው:: ተመስጦ የተሠወረው ተገልፆ እንዲታይህ ከጥልቁ ምሥጢር ተካፋይ እንድትሆን ´የሚያደርግህ እንደሆነ ዘወትር አስታውስ:: ተመስጦ ከባዶነት ጠብቆ ለውሳጣዊት ነፍስህ መንፈሳዊ ምግብ እና እግዚአብሔር ያደረገልህን ድንቅ ሥራ ሁሉ የምታስብበት ጥበብ ይሠጥሀል::

## ተፈጥሮ

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለአብርሃም ልጅ ይስሐቅ የተነገረው፣ ሌላውን የተመስጦ ዓይነት ማለትም በተፈጥሮ መመሠጥን ሊያመለክት ይችላል:: «ይስሐቅም በመሸ ጊዜ በልቡ እያሰላሰለ ወደሜዳ ወጥቶ ነበረ::» (ዘፍ 24:63):: ይህ ማለት በተፈጥሮ ውበት መማረክና መመሠጥ ሳይሆን ቅዱስ ዳዊት እንዳለው ከሚያስገኘው መንፈሳዊ ጥቅም አንጻር ነው:: «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ:: የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል......» (መዝ 18:1)::



www.ethiopianorthodox.org

በተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ፈጣሪነት እንዲሁም ለፍጥረቱ ካለው ከፍተኛ ጥንቃቄ የተነሳ ጽኑ ፍቅሩን ወደማሰብ ትሸጋገራለህ::

ይህ በዐይን የምታየው ሰማይ ታላቅ የተመሰጠ ዓለም ሊሆንህ ይችላል ስለእግዚአብሔር ዙፋን ማሰብ ነውና:: (ማቴ 5:34)::

የሐንስ ፍቁረ እግዚእ በራዕይ መጽሐፉ ስለዚህ ነገር አብዝቶ ይናገራል:: በተለይ (በራዕይ 4:1) «ከዚያ በኋላም አየሁ:: እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ....» እንዲሁም (በራዕ 21) ላይም ስለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትና እግዚአብሔርና ሰዎች በአንድነት ስለሚያድሩበት ሥፍራ በተመስጦ እየተመለከተ ይናገራል::

ሕሊናን በሰማያትና በሰማያዊ ነገር ላይ መስቀልና መመሠጥ ያለ ጥርጥር የአንድን ሰው አእምሮ እና ልብ ከቁስ አካላዊ (ማቴሪያላዊ) ደረጃ ከፍ ያደርገዋል:: በሰማያት መመሠጥ በመላእክት መመሠጥን ያመጣል:: በተጨማሪም በሰማያት ኃይሎች ሁሉ፣ ኪሩቤልን፣ ሱራፌልን፣ ሊቃነ መላእክትን በመንበሩ ፊት ያሉትን እልፍ፣ አእላፍ የሚሆኑትን ሠራዊት፣ ሰውን ለማገዝ፣ ለመርዳት የሚላኩትን ሁሉ እያሰቡ ፈጣሪን በተሠቀለ ሕሊና መመልከት ነው:: (ዕብ 1:14)
«ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?»

እነዚህ መላእክት ባህርያቸው ምንድን ነው? መንፈሳዊነታቸው፣ ቅድስናቸው፣ ፍቅርና መታዘዛቸው እንዴት ነው? (መዝ 103:4)፣ ለሰዎችና ለእግዚአብሔር የሚሠጡት አገልግሎትስ ምን ዓይነት ነው? በዘለዓለም ሕይወት ውስጥ ከእኛ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን ይሆናል?.... በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ መዋኘት፣ መንሳፈፍ ይሉሃል ይህ ነው! «....ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ የልጅሽን የባህሩን ጥልቀት ሊዋኝ ይወዳል፣ የወዳጅሽ የመሠወሪያው ማዕበልም ያማታዋል::



ዳግመኛም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናዬ ተሠውሮ ወደላይ ወጥቶ የሕያው መሠወሪያ የሆነውን ሊገልጥ ይወዳል:: ከነደ እሳትነቱ የተነሳ ይፈራል ከዓየራት ከእርሷቸው እርቦ አይደርስም::..........» (ቅዳሴ ማርያም 84፣85)::

አባ ሕርያቆስ የእመቤታችን እናትነትና ድንግልና፣ አምላክን በማህጸኗ መሸከም፣ ታላቅ ተመስጦ ሆኖት ይህን የእግዚአብሔር ድንቅ ጥበብ ለመረዳት የተጓዘበትን ጉዞ ሲናገር ይቆይና «....አቅቶት ወደቀደመ አኗኗሩ ይመለሳል» ይላል::

ለአንተም ይህ ሁሉ ነገር ጥልቅና ከባድ ቢሆንብህ ከዚህ ዓለም በተለዩ ነፍሳት መንፈስ ልትመሠጥ ትችላለህ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለአባታችን አብርሃምና በእቅፉ ስላለው አልአዛር እንደነገረን በገነት ከእግዚአብሔር ጋር ባሉ ቅዱሳን (ሉቃ 23:43)፣ ወይም በምድር ለረድኤት በታላኩት መነሻህን ልታደርግ ትችላለህ:: አንድ ኮከብ ከሌላው በክብር እንደሚለይ ለእያንዳንዳቸው የተሠጠው ክብርም ሊመስጥ የሚችል ነው:: (1 ቆሮ 15:41)::

ትንሳኤ ሙታን፣ ሰማያዊውና መንፈሳዊው አካል (1 ቆሮ 15:42-50)፣ ዘለዓለማዊነት፣ የሚመጣው ክብር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ክብረ ቅዱሳን፣ ለዘለዓለም ደስታ እንዲሆን ለእኛ የተዘጋጀልን መንግሥት.... እነዚህ ሁሉ በተመስጦ ወደእግዚአብሔር ለመጓዝ እንድንችል የሚያነሳሱ ናቸው::

ይህም ከከበደህ ደግሞ ወደምድር ተመለስና በዙሪያህ ያሉትን የተፈጥሮ ጸጋዎች አሰላስል:: ጌታችን እንደተናገረው «የሰማይ ወፎችን፣ የሜዳ አበቦችን ተመልከት» (ማቴ 6:26-30):: አምላክህ ክርስቶስ ያስተማረህ ስሜትን የሚቀሰቅስ ሥጋዊ ተመስጦ፣ ውበትን፣ የቀለሞችን ቅንጅት፣ መዓዛቸውን እያደነቅህ፣ ስምምነታቸውን እያየህ ብቻ የምታልፍበትን አይደለም:: ከስሜታዊነት በላይ ከፍ ብለህ ንጉሡ ሰሎሞን እንኳን በዚህ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደአንዱ ያልለበሰውን ዓይነት አድርጎ የፈጠራቸው እግዚአብሔርን አስበህ ሕሊናህን ለእርሱ እንድታስገዛ ነው:: በዚህ



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ከሆንክ ለእነዚህ ሁሉ ፍጥረታት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያስብላቸው ታሰላስላለህ:: አንተም ራስህ «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል፣ በእርሱም እመካለሁ» ወደሚል ጽኑ እምነት ታድጋለህ:: ጭንቀት፣ ጥበት፣ አለመረጋጋት፣ ሰላም ማጣት፣ ብቸኝነት ሁሉ ከአንተ ይርቃሉ::

በተፈጥሮ አበቦችና በሰው እጅ በተሠሩት (artificials) መካከል ያለውን ልዩነት በተመስጦ ካስተዋልክ፣ ሰው ምንም ያህል ቢጠበብ ሕይወት ሊሠጥ የማይችል መሆኑን፣ ያለሕይወት መዓዛና እድገት ያለመኖሩን ትረዳለህ:: መልካቸውም ቢሆን በፍጹም ሊነጻጸር የማይችል ስለሆነ ሁሉን የሚችል ጌታህን ሥራዎች ለማድነቅ መንገድ ታገኛለህ:: በሰማይ ወፎችም እነዚህን ሁሉ ማስተዋል ትችላለህ:: በተፈጥሮ ተነስተህ ፍ...መስጠ ወደእግዚአብሔር ስትደርስና፣ ከዓለም ስታመልጥ ደግሞ «ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች፣ ወጥመድ ተሠበረ፣ እኛም አመለጥን» እያልክ በደስታ ትዘምራለህ:: (መዝ 123:7)

በእውነት እግዚአብሔርን ምን ቃል ይገልጸዋል? ለሚጠሩት ሁሉ ምግባቸውን ይሠጣል:: ሰማይን በደመና ይሸፍናል:: ምድርን ተጠምታ ሳለች በዝናም ያረሠርሳታል:: ለእንስሳትም ሳርን በምድር ላይ ያበቅላል:: ለሰው የሚጠቅመውን ሁሉ ያዘጋጃል:: (መዝ 146:9)፣ እርሱ ራሱም «ቁራዎችን ተመልከቱ፣ አይዘሩ፣ አያጭዱ፣ ዕቃ ቤትም ጎተራ የላቸውም:: እግዚአብሔር ይመግባቸዋል» ሲል ተናግሯል:: (ሉቃ 12:24)

አሁን ስለቁራ ስናስብ በውስጣችን ያለው ምስል ጥሩ አይደለም:: እንደ መጥፎ እጣም የሚቆጥሩት ብዙ ሰዎች አሉ:: እግዚአብሔር ግን ይህን የመሠለ ጥንቃቄ ያደርግለታል:: ከዚህም በላይ በዚያ የረሀብ ዘመን ላይ ለኤልያስ መጋቢ እንዲሆነው ተመድቦም ነበር:: (1 ነገ 17:6):: በገድለ ቅዱሳንም ለባህታዊው ጳውሎስ ምግብ ሲያመላልስለት ስታይ እግዚአብሔርን ዕጹብ ዕጹብ ያሰኝሃል:: እግዚአብሔር እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ ፍጥረታቱን፣ ወደቅዱሳኑ ይልካቸዋል:: እነርሱም መታዘዝንና ፈቃዱን መፈጸምን ያውቁበታል:: በእነዚህ ሁሉ የተገለጸውን የእግዚአብሔር ክብር



ስታነብ ባዶ ከሆነው የመጀመሪያ ሀሳብህ ወደጥልቁ መንፈሳዊነት በተወሠኑ ደረጃዎች መሻሻል ታደርጋለህ::

እግዚአብሔር በጥቃቅን ነፍሳት ሳይቀር ያስተምርሃል:: ብዙ መንፈሳዊ መንገዶችንም አዘጋጅቶልህ በእነዚህ ወደ ፈጣሪህ ተጉዘህ ትደርስ ዘንድ አድርጎሃል:: «አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ፣ መንገዱንም ተመልከተህ ጠቢብ ሁን....» (ምሳ 6:6):: በሕይወቴ አንድም ጉንዳን ሥራ ፈት ሆኖ አይቼ አላውቅም:: ባለማቋረጥ ይሮጣል፣ ይሠራል፣ አይቆምም::

ገብረ ጉንዳንን በማስተዋል ላሰበው፣ ሕብረታቸውን፣ ከመጠናቸው አስር እጥፍ የሚሆን ነገር ተሸክመው ሲጓዙ ለተመለከተ አስገራሚ ትምህርት ይሰጣሉ:: የሕብረት ሥራን፣ ሥነ ሥርዓት፣ እንዲሁም መስመራቸውን ጠብቀው ሲጓዙ፣ ሕግና ሥርዓት መከተልን ያስተምራል:: በመካከላቸው የሚታየው ድንቅ የሆነ መግባባትም ፍቅርንም ያሳስባል:: እንደዚሁ ንቦችም ብዙ ሊያስተምሩ ይችላሉ::

አስደናቂው የንቦች አኗኗርም ሌላው ሊመስጥ የሚችል ዓለም ነው:: እግዚአብሔር እንዴት ንቦችን ከዚህ ተሠጥኦና ችሎታ ጋር ፈጠራቸው? የአበባን ጹቄት ሰብስቦ እጅግ የሚጥም ማርን መስራት የሚገርም ነው ያን አስገራሚና በእውቅ ዲዛይነር የተሰራ የሚመስል ሰም የሚሰሩትስ እንዴት ነው? አበባን ፍለጋ የሚጓዙት ርቀትም አስደናቂ ነው:: ስለዚህ እነዚህን አስገራሚ ፍጡራን የፈጠረ እግዚአብሔር ሥራው ምን ያህል ድንቅ ነው?

መንፈሳዊ ሰው ትንሽ ምክንያትን አንስቶ ወደጥልቅ መንፈሳዊ ዓለም የመግባት ችሎታ ያለው ነው:: ከዚህም በላይ ቁስአካላዊ ከሆነው ነገር መንፈሳዊውን ትምህርት ለይቶ ማውጣት የሚችል ነው::

የሰው አካልም የፈጣሪን ታላቅነት የሚያስረዳ በመሆኑ ሠፊ የተመስጦ ዓለም ሊሆን ይችላል:: የእያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ልዩ ችሎታ አስተዋይን ሰው የመመሠጥ በቂ ኃይል አለው:: ለምሳሌ



www.ethiopianorthodox.org

የአእምሮአችን የማየት፣ የመስማት የእንቅስቃሴና የንግግር አስገራሚ መዕከሎቹ፣ ከእነዚህ ለአንዱ ማዕከል የደም ዝውውር ቢቋረጥ የሚከሰተው ነገር እንዴት አይመስጥ!

መጠኗ የእጅ ጭብጥን የምታክለውን ልብንና ሥራዋንም ብናስብ እንደዚሁ ነው:: እንደመጠኗ ሳይሆን እጅግ በጥንቃቄ የሚከናወኑ ውስብስብ ተግባርት ይከናወኑባታል:: ልብ በአእምሮ እንደሚወሰን፣ ሕይወትም በልብ እንቅስቃሴ ሥር ነው:: ስለሰውነት ክፍሎቻችን ሁሉ አንስተን ርቀታቸውን፣ ሥራቸውን ብንተነትን ጊዜም ሁኔታዎችም አይፈቅዱልንም:: እነዚህ ሁሉ ግን በአንድ ሰውነት ውስጥ በስምምነት መሥራታቸው ዕጹብ ድንቅ የፈጣሪ ሥራ ያሠኛል:: ከእነዚህ አንዱ እንኳን ከጥቅም ውጪ ቢሆን ዛሬ ያለው የረቀቀ የሳይንስ ጥበብ እንኳን ወደቀድሞ የተፈጥሮ ሁኔታው ሊመልሰው አይችልም::

ታዲያ እነዚህ ሁሉ በሁሉን ቻይ አምላክ የሆኑ የሰውነት ክህሎቶች ከሆኑና ይህን ያህል የሚያስደምሙ ከሆኑ የመንፈስ ስጦታዎች ምን ያህል ይረቅቁ ይሆን?

## በክስተቶች /በድርጊቶች/ መመሠጥ

ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ጥበብና ዕቅድ፣ ሀሳቡን እንክብካቤውን የሚገልጹ በዕለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ የሚከሠቱትን ነገሮች በማሰብ መመሠጥና ወደእግዚአብሔር መጓዝ ማለት ነው:: ያለንበትንና በታሪክ የምናውቀውን የእግዚአብሔር እጅ ያለበትን ነገር ሁሉ የሚያጠቃልለውም የዚህ ዓይነቱ ተመስጦ ነው::

ታሪካዊ ሁኔታዎችን ቆም ብለህ ሳታሰላስል በግድ የለሽነት ብታልፋቸው ለመንፈሳዊ ሕይወትህ መልካም አይሆንም:: በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሕያው ሆኖ የሚኖር እንጂ አለፈ የሚባል ታሪክ የለም:: ምክንያቱም የሆነውን ሁሉ ያከናወነው ትናንት የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ወደፊትም ዒኖር ዘለዓለማዊው አምላክ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው::



በአርዮስ ላይ በተወሰደው እርምጃ የእግዚአብሔር እጅ ነበረ:: ዲዮቅልጥያኖስና ኔሮን በደረሰባቸው ቅጣት ላይ ሁሉ እግዚአብሔር ነበረ:: አትናቴዎስን ዓለም ሁሉ በጥላቻ በተነሳበት ጊዜ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ነበረ:: እግዚአብሔር ከአባቶቻችን ቅዱሳን ጋር የሠራና ከሞታቸው በፊት ታሪካቸውን እንዲያቆዩልን ያስቻላቸው ነው::

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የታጣበት ጊዜ የለም:: በእርግጥ ታሪክ የድርጊቶች መዝገብ ወይስ አምላካዊ ትምህርት? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ፍጹም የሆነ ተመስጦ ያስፈልግሃል::

በ313 ዓመተ ምሕረት፣ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ፣ ለሃይማኖት ነፃነት የሚሠጥ ዐዋጅ ሲታወጅ እግዚአብሔር ንጉሡን እንዴት እንደተጠቀመበት የሚጠይቅ ተመስጦ አይመጣም? ይህ ታሪካዊ ጊዜ በክርስትና ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራ ያለውና የክርስቲያኖች ስደት ወደማብቃቱ የመጣበት ጊዜ ነው::

በዓለም ላይ የተፈሩ፣ የተከበሩ ኃያላን በሚያስደንቅ ፍጥነት ሲወድቁና ሲወገዱ፣ በሚከሠተው ነገር ውስጥና በወደፊት እጣቸው ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ አልነበረበትም ብሎ መካድ ይቻል ይሆን? ታሪክን ከእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ መለየት መንፈሳዊ ተግባር አይደለም:: ስለዚህ መንፈሳውያንን በታሪክ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር እጅ በእጅጉ ይመስጣቸዋል::

## በጸሎት መመሠጥ

በጸሎት ውስጥ የሚመጣው ተመስጦ፣ በግል ወይም በማህበር ጸሎት ወይም በቅዳሴ ሊሆን ይችላል:: ጸሎቱን በተመስጦ የጀመረ ሰው ጸሎቱ ጥልቅና የማስተዋል ብሎም ስኬታማ ይሆንለታል::



www.ethiopianorthodox.org

አባቶቻችን ቅዱሳን የጸሎት ቃላትን በከንቱና ጥልቅ ባልሆነ መንፈስ ፈጥኖ ለመጨረስ ብቻ አይደግሙም ነበር:: ምክንያቱም በዚህ በአፋቸው ውስጥ ካለው ጣዕመ ቃል የተነሳ አቋርጠው ወይም ፈጥነው ጨርሰው ሌላ ነገር ሊናገሩበት አይፈልጉም:: የጸሎት መንፈሳቸው በሚሰጣቸው ኃይልና ጥንካሬ በተመስጦ ወደእግዚአብሔር ተጉዘው በማስተዋል ይጸልያሉ:: ቃላቱ የሚፈልቁት ከልባቸው መዝገብ ስለሆነ ሀሳባቸውና ቃላቸው የተለያየ አይደለም:: በፊቱ ከቆሙት ከእግዚአብሔር ጋር ስለመነጋገራቸው እንጂ ስለጸለዩበት ሰዓት መርዘምና ማጠር አይጨነቁም:: ብዙውን ጸሎት በፍጥነት በመጨረሳቸው መልካም የጸሎት መስዋዕት እንዳቀረቡ ደስ የሚላቸው ሰዎች አሉ:: ማር ይስሐቅ አንተን ሲመክርህ እንዲህ ይላል:: «አንተ ግን ለቃላት ቆጠራ በእግዚአብሔር ፊት አትቁም::»

በተመሳሳይ መልኩ ለመንፈሳዊ መዝሙርም እንደጸሎት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ከመንፈሳዊነት የወጡና አላማቸው እግዚአብሔር ያልሆኑ ማናቸውም ነገሮች ከተመስጦ ውጪ ስለሚሆኑ ከንቱዎች ናቸው::

በጸሎት፣በመዝሙር፣ የመመሰጥ ስጦታ ከሌለህ ደግሞ የአባቶቻችንን የጸሎትና የመዝሙር ተመስጦ ከገድላቸው እንድትማር እመክርሃለሁ::

## በእግዚአብሔር ባህርያት መመሰጥ

ስሙ የተመሰገነ ይሁንና የእግዚአብሔር ባህርያት ጥልቅ የተመስጦ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ:: የምሕረቱ ብዛት፣ የቸርነቱ ስፋት፣ የትዕግስቱ መጠን..... የአምላካችን የክርስቶስ ርህራሄ፣ ፍቅር፣ ኃጢአተኞችን በይቅርታ ዓይን መመልከት......ይህን ሁሉ እያሰላሰልክ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» እያልክ ብታመሰግነው ባህርያቱ በተመስጦ ውስጥ ወደእርሱ እንድትጓዝ ያደርጉሃል::

በእግዚአብሔር ባህርያት ላይ ተመስርቶ የሚመጣውን ተመስጦ በሁለት መንገድ ልታየው ትችላለህ:: የመጀመሪያው፣ ከላይ የተመለከተው ከእኛ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር የሚገለጸው ሲሆን ሁለተኛው የራሱን ባህርያት የሚገልፅ ነው:: ለምሳሌ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊነት፣ ወሰንየለሽነት፣ ፈጣሪነት፣ ኃያልነት፣ እያሰብክ መመሰጥ ማለት ነው::

እነዚህ ሁሉ ክርስቲያን በንጹሕ መንፈስ ወደ ንጹሕ አምላካችን ወደእግዚአብሔር ሊጓዝ የሚችልባቸው መንገዶች ናቸው::

ኃጢአተኞች ሳለን ሳይንቀን ወደእርሱ ለመድረስ እንድንችል እነዚህን መንገዶች ያዘጋጀልን አምላችን እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ስም የተከበረና የተመሰገነ ይሁን::

አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ተርጓሚ
ዲያቆን ግርማ ባቱ
በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የ3ኛ ዓመት የዲግሪ ተማሪ